በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 8

## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ሚያዝያ ፲ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 8

## መረዳት

- የትዳር አጋራችንን መረዳት በጊዜ ወይም በአጋጣሚ ሊከሰት የሚችል ክስተት ስላልሆነ ብዙ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡
- ከትዳር አጋራችን ጋር ውጤታማና ጤናማ የሆነ ግኑኝነት እንዲኖረን ሁሉን አቀፍ ውሳኔ በመወሰን አንዳችን ሌላውን ለመረዳት ቅርበታችንን ማጥበቅ ይጠበቅብናል፡፡
- ባልም ሆነ ሚስት ፍጹም የተለያየ ከሆኑ አስተዳደግ፣ የቤተሰብ ልማድና ባሕል፣ የትምህርት መስክ፣ ማኅበራዊ ልምዶች፣ ጓደኞችና የሕይወት ልምዶች የተገኘን መሆናችንን መገንዘብ ይገባናል፡፡
- ስለዚህ የትዳር አጋራችንን የት መጣና ልምዶች በአግባቡ በመመርመር በግልጽ መረዳት ይኖርብናል፡፡ ይህም የትዳር አጋራችንን ምኞት፣ ፍላጎትና፣ ጠባይ በአግባቡ እንድንረዳ ከመርዳቱም በላይ ያሉትን ሁኔታዎች ተቀብለን አብሮ ለመኖር ዝግጁ ለመሆን ያበቃናል፡፡
- በተጨማሪም በወንድና በሴት መካከል ያሉትን የተለያዩ መፈላለጎች በመረዳት ተቀብለን እናስተናግዳቸውና በጥረቱም የጋራ ከሆነ ትዳራችንን ውጤታማ ማድረግ ያስችለናል፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 8

**መረዳት**

**በወንዶችና በሴቶች መካከል ያሉ ዋና ዋና ልዩነቶች፡-**

- ሴቶች በይበልጥ በልባቸው ሲደገፉ ወንዶች ደግሞ አእምሮአቸውን የበለጠ ያምናሉ፡፡
- ሴቶች ለዝርዝር ጉዳዮች ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያደርጉ ሲሆኑ ወንዶች ግን ጉዳዩን በጠቅላላ (በመላ) በአንድ ላይ ይመለከቱታል፡፡
- ሴቶች ርኅራኄን የሚሹ ሲሆኑ ወንዶች ደግሞ መከበርን ይሻሉ፡፡
- ሴቶች በሚሰሙት የሚገፉ ሲሆኑ ወንዶች ደግሞ በሚያዩት ይገፋሉ፡፡
- ሴቶች መታቀፍ የሚፈልጉ ሲሆኑ ወንዶች ደግሞ አመክንዮ ይፈልጋሉ፡፡
- ሴቶች ተከታታይነት ያለው ክብካቤና ፍቅርን ማየት (መመልከት) የሚሹ ሲሆኑ ወንዶች ደግሞ ክፍተቶችን/ነጻነትን ወይም እረፍትን ይፈልጋሉ፡፡
- ላቀ ያለ መረዳት የበለጠ መቻቻልን፣ እርስ በርስ መቀባበልን እንዲሁም የገዛ ፍላጎታችንን ስለሌላው መሥዋዕት ማድረግ ብሎም ለሌላው በጎውን መመኘት እያቆጠቆጠ እንዲያድግ ያደርገዋል፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 8

## ራእይ

- በወንድና በሴት መካከል የሚፈጠረው አንድነት ምንጩ እግዚአብሔር ለሰው ያቀደው እቅድ ነው።
- ‹‹እግዚአብሔር አምላክም አለ፦ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት።እግዚአብሔር አምላክም የምድር አራዊትንና የሰማይ ወፎችን ሁሉ ከመሬት አደረገ በምን ስም እንደሚጠራቸውም ያይ ዘንድ ወደ አዳም አመጣቸው አዳምም ሕያው ነፍስ ላለው ሁሉ በስሙ እንደ ጠራው ስሙ ያው ሆነ። አዳምም ለእንስሳት ሁሉ፥ ለሰማይ ወፎችም ሁሉ፥ ለምድር አራዊትም ሁሉ ስም አወጣላቸው ነገር ግን ለአዳም እንደ እርሱ ያለ ረዳት አልተገኘለትም ነበር።እግዚአብሔር አምላክም በአዳም ከባድ እንቅልፍን ጣለበት፥ አንቀላፋም ከጎኑም አንዲት አጥንትን ወስዶ ስፍራውን በሥጋ ዘጋው።እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት ወደ አዳምም አመጣት። አዳምም አለ፦ ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፥ ሥጋም ከሥጋዬ ናት እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል።ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። አዳምና ሚስቱ ሁለቱም ዕራቁታቸውን ነበሩ፥ አይተፋፈሩም ነበር።›› ***ዘፍጥ 2፡18-24።***

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 8

## ራእይ

- እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን የነበረው የመጀመሪያ እቅዱ ከእርሱ ጋር በደስታ እንዲኖሩ፣ በትዳራቸውም ደስ እንዲሰኙ፣ ልጆችን ወልደው ዓለምን እንዲሞሉ፣ ለዘላለም በሰላም ተደስተው እንዲኖሩ ነበር፡፡ በክርስቶስ ወደ ቅዱስ ጋብቻ ሕይወት የሚገቡ ሁሉ እንዲኖራቸው የሚያስፈልጋቸው የሚታደሉትም ይኸንኑ ነው፡፡
- ሙሽሮቹ ጸሎተ ተክሊል ሲፈጸምላቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡም ሆነ ተፈጽሞላቸው ሲወጡ የሚያደርጉት የእግርጉዞ የሚያመለክተው በሕይወታቸው የሚያደርጉትን ጉዞ ነው፡፡
- ጋብቻቸውም እርስ በርሳቸው የሚረዳዱበት፣ እግዚአብሔር የሚሰጣቸው ልጆችም እግዚአብሔርን አውቀው በአንድነት ወደ ዘላለማዊ ሕይወት እንዲደርሱላቸው ደጅ የሚጠኑበት የሚናፍቁበት ነው፡፡
- ምስጢረ ተክሊል የሚፈጸምላቸውም ለእግዚአብሔርና እርስ በርሳቸው ታማኝ ሆነው በመኖር ዘላለማዊ ሕይወትን በመውረስ የምድር ኑሮአቸውን እንዲደመድሙ ነው፡፡
- ይህ እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸው ራእይም ወደ ዓላማዎችና ግቦች መለወጥና ተጋቢዎቹ በሕይወታቸው አኑረውት ለመፈጸም የሚጣጣሩት መሆን አለበት፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 8

## ራእይ

- ባለ ትዳሮች ራእያቸውን፤ ግባቸውን ለመምታት ወደሚያስችላቸው ወደ ተግባራዊ እቅድነት ቢለውጡት እጅግ የሚወደድና የሚደነቅ ነው፡፡
- ባለትዳሮች መንፈሳዊና ዓለማዊ ሕልሞቻቸውንና ግቦቻቸውን እውን ሆነው ለማየት እንዲችሉ ዕቅድና መልካም የትዳር አስተዳደር ስልት እንዲኖራቸው ያስፈልጋቸዋል፡፡
- የትዳር የመጀመሪያውና ከሁሉ የላቀው ግቡ መንግሥተ ሰማያትን መውረስ ነው፡፡ ‹‹ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል፡፡›› *ማቴ 6፡33፡፡* በሕይወታችን ግባችን እውን ሆኖ እንድናየው የሕይወታችንን ዕቅድ ሁሉ በዚሁ መንገድ በማዘጋጀት ከሁሉም የላቀ ቦታ እንስጠው፡፡
- ሁለተኛውና ባለትዳሮች እንዲኖራቸው የሚያስፈልገው ስኬታማ፣ ደስተኛና የተረጋጋ ትዳር ነው፡፡
- ባለትዳሮቹ አብረው ተቀምጠው ይኽን ሰፊ ግብ በጊዜ ተምነው ሊያሳኩት ወደሚችሉበት እቅድ መለወጥና በታቀደለት ጊዜ እንዲፈጸም ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ለምሳሌ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ልጅ መካከል ያለውን የዕድሜ ክፍተት ሁለት ዓመት እንዲሆን ሊያቅዱ ይችላሉ፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 8

## ራእይ

- እንዲሁም ባለትዳሮቹ ውሱን፣ የሚለካ፣ ሊያሳኩት ወይም ሊደርሱበት የሚችሉት፣ ትክክለኛ ግብን በተገቢው ጊዜ ማዘጋጀት ያስፈልጋቸዋል። (S.M.A.R.T = Specific, Measurable, Achievable or Attainable, Realistic and Timely).
- ይህን ዕቅድ ከትዳር አጋር ጋር ለማውጣት ብዙውን ጊዜ አብረን ማሳለፍ፣ አብረን ማሰብ፣ ነገሮችን በአግባብ መነጋገር፣ መስማማትና ውሳኔዎችን መወሰን ያስፈልገናል፤ ይህም በመካከላችን ጠንካራ ግኑኙነትና መግባባት እንዲኖር የሚያደርግ ጥሩ አጋጣሚ ነው።
- እቅዳችንንም እንዴት እንደምናሳካ ቅደም ተከተሎቹንና በመንገዳችን መካከል የሚኖሩ ለውጦችን እንዴት እንደምናጣጥም ማወቅ ይጠበቅብናል።
- ግብንና እቅድን ከማዘጋጀት ጋር አብሮ የሚሄደው ሌላው ጉዳይ የሥራ ድርሻን መከፋፈልና እንደተሰጠንም የየራሳችንን ድርሻና ኃላፊነት መወጣት ነው። ግባችን የተሳካ እንዲሆን ማን ምን እንደሚሠራ መታወቅ አለበት።
- የሥራ ክፍፍሉም ሚዛናዊ መሆን ይኖርበታል። ምክንያቱም አንዱ ከፍተኛ ጫና በዝቶበት ሲሠራ ተቀምጦ በውጤቱ የሚዝናናና ተጨባጭ አስተዋጽኦ የማያደርግ መኖር ስለሌለበት ነው።

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 8

## ራእይ

- ዋናውን መንፈሳዊ ግባችንን በማሳካት - እኛም ሆንን ልጆቻችን ዘላለማዊ ሕይወትን ይወርሱ ዘንድ በመረዳዳትን/በመርዳት - ዓለማዊ ግባችንን በማሳካት መካከል ሚዛናችንን ጠብቀን መንቀሳቀስ እንደሚያስፈልገን ፈጽመን መዘንጋት አይገባንም፡፡
- ይህንም ሚዛን ጠብቀን እንድንቀሳቀስ ሊያደርገን የሚችለው ጥሩ እቅድ፣ ጥበብ የሚላበት የጊዜ አጠቃቀም፣ ተከታታይነው ያለው ግምገማ፣ ጥበብን የተሞላ ውሳኔና ኀሊናዊ ምርጫ ነው፡፡
- ‹‹ራእይ ባይኖር ሕዝብ መረን ይሆናል፡፡›› *ምሳ 29፡18፡፡*

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org